# ወለል እንደ ተልባ !

ከዓሣዬ

በእባብ መርዝ ምላሱ ቅርሻት እየቀራ
ያልሆነውን ሁኖ በዘርዛራው ጥርሱ ፡ ሸርከት እየዘራ ፡
ኢሕኣፓ ኣለ እንዴ ? ኢሕኣፓኮ ኣረጀ ፡ ኢሕኣፓማ ሞተ
ብሎ ሲዘላብድ የባጡን የቆጡን እየወሸከተ
በትግል ጽናትን ፡ በጽናት መሞትን እየወነጀለ
በሥልጡን ፖለቲካው ፡ ያገር ጥቅምን ሸጦ ለባዕድ ያደረ ፡
ሃቁ ይታይ ሲባል ፡ ሁሌም እንደ ተልባ ወለል ሸርተት ያለ
ወደ ማጡም ሲዘቅጥ ፡ ዐይኑ እንደፈጠጠ በሚዛን ሲለካም ፡ ከላባ ቀለለ ።

ይኼ ውርደት ጌጡ ፡ ለባዕድ ጌቶቹ ለተገንጣይ ኣድሮ
ባንዳ ኣንጃ ፋሺሥት ፡ በታኝና ጠባብ ዞሪያውን ኮልኩሎ
የኣገሩን  መገንጠል ፡ ያለ ሕዝቡ ፈቃድ ፡ በኣሥር ጣት ፈርሞ ፡ በኣሻራው ኣትሞ
የኣንድነት ሃይሎችን ፡ በባዕዳን ትዕዛዝ ኣልያችሁ ብሎ
ሲያቅራራ ሰማነው ፡ ለኣገር ቆምኩ እያለ
ዲያሥፖራን ሲያሣምን ፡ የባጡን የቆጡን እየቀባጠረ ።

ውሸት እንደ ጣቃ እየተረተረ ፡ ከጠላት ወግኖ
ኢትዮጵያን ሲያሥበትን ፡ ወገንን ሲያሣርድ ፡ የእንግሊላ ኣጋድሞ
የኣገር ጥቅም ሲነካ ፡ ሁሌም እንደ ተልባ ወለል ሸርተት ብሎ
ቢመከር ፡ ቢዘከር ፡ ኣሻፈረኝ ብሎ ፡ ከሃቅ ጋር ተጣልቶ
ልጆቼኮ ናችሁ ፡ መሣሪያው በእጃችሁ ፡ ብሎ ተፈጣጥሞ
ኣገር ኣሥፈረሰ ፡ ወገን ኣሥጨረሰ ፡ ኣቶ ፕሮፌሰር ለከርሱ ኣድልቶ ።

በኣንድ ለኣምሥት ጠርናፊት ተቀይዳ ኣገር
በዘርፈ ብዙ ጠላት በደም መጣጭ መዥገር
ዋለልኝ ሲወገዝ ፡ ታጋይዋ ሲሣደድ ፡ ኣዳኝዋም ሲገደል ፡
በጽናት መታገል ፡ በተገላቢጦሽ እንደ ነውር ሲቆጠር
በኣንፃሩ ገዳይዋ ፡ እንደ በኩር ልጅዋ ተሹሞ ሲከበር ፡
የሥር ነቀል ለውጡ ፡ ግቡን እንዳይመታ ጋሬጣ እየሆነ
ግፍ ሞልቶ ሲፈሥ ፡ ኣሥርተ ዓመታቱ  ሥለተቆጠረ
እሥቲ ኣደብ እንግዛ ! ዳግም ኣንታለል ! ወለል ሸርተት ባለ
ትውልድ እንዳይረግመን ፡ በኣደራ በላነት እየወነጀለ
ኣዎ ! ታሪክ እንዳይወቅሰን ! ታሪክ እንዳይረግመን ! በኣደራ በላነት እየወነጀለ ! ።

October 11/2015 G C.